# የህዝባዊ ወያነ ሀርነት ትግራይ ርዕዩት፣
# የአካባቢ ተኮር የፖለቲካ ድርጅቶችና፣
# የነገ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግር፤

## ( ክፍል አንድ )

ይነጋል በላቸው

አሁን ሀገራችን ላለችበት የፖለቲካ ቀውስ መፍትሄ ለማግኜት ሁላችንም በያለንበት እንጥራለን። በላያችን ላይ ያንዣበበው ይህ ቀውስ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ፤ ከያንዳንዳችን የሚቀርቡት መፍትሄዎች ከአፅናፍ አፅናፍ ያዳረሱ ናቸው። እናም ያልተዳሰሰ ሰፈር፣ ያልተወረወረ መላ፣ እና ያልተቀየሰ መሥመር አለ ብሎ መናገር ያስቸግራል። የሚቀርቡት መፍትሄዎች፤ ማዕከላዊ መድረክ ባለመኖሩ፤ በውል ተወያይተንባቸው፤ በጎና በጎ ያልሆነ ጎናቸው ተመዛዝነው፤ ከመደምደሚያ ላይ የተደረሰባቸው የሉም። ትግሉ የተበታተነ ነው። መፍትሄ አፈላለጉም ሆነ መፍትሄ ፈላጊውም እንዲሁ። በዬድርጅቱ የተሠባሰቡት፤ የዬድርጅቶቻቸውን መፍትሄ አንግበው ያለዚህ ሌላ አታንሱብን ይላሉ። ትግሉን ከጥናትና ምርምር አንፃር የሚመለከቱት ምሁራን ደግሞ መሆን ያለበት እንዲህ ነው በሚል መነፅር ያልተዛምዶ መፍትሄ በየድህረ ገፁ ይለፋሉ። የአካባቢ ተኮር ድርጅቶች ደግሞ ያካባቢያቸውን ችግር የተለዬ አድርገው በመፈረጅ፤ ውስንና ጠባብ አጀንዳ ውስጥ ተዘፍቀዋል። በዚህ መሐል የገዢው ቡድን ችግራችንን እያራገበውና እያባባሰው ነው። ምርጫ የሌለውና አንድዬ መፍትሄው፤ ***የአንድነት ኃይሎች መሠባሰብ*** መሆኑ እንደተጠበቀ እያለ፤ በዙርያው ካሉት የመወያያ ርዕሶች አንዱን በዚህ *"ክፍል አንድ"* በማንሳት መንደርደሪያ አቀርባለሁ። የዚህ ፅሑፍ ማዕከላዊ ነጥቡ በአካባቢ አተኩረው የተዋቀሩና ይኼንኑ የመጨረሻ ግባቸው ያደረጉ ድርጅቶች፤ በሀገር አቀፍ ለሚደረገው የፖለቲካ ትግል ዕንቅፋቶች መሆናቸውን ማመልከት ነው። *"በክፍል ሁለት"* እና *"ክፍል ሶስት"* ደግሞ የትጥቅ ትግሉን አስመልክቶና የትግል ታሪካችንን እዳስሳለሁ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የተለያዬ ቋንቋ ተናጋሪዎች፤ ወይንም በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ከሚኖሩ ክፍሎች ካንዱ ወይንም ከተደባለቀው ተወልደናል። ያደግንበት አካባቢም፤ ያነገብነውን ያመለካከት መሠረት ሠጥቶናል። በዚህ በየዕለቱ እዬጠበበ በሚሄደው ዓለም ደግሞ፤ ኢትዮጵያዊነታችን አስተሣሥሮ የያዘን የማንነታችን ዓምድ ነው። ኢትዮጵያዊነት በማንነታችን የታደልነው ፀጋ ነው። ኢትዮጵያዊነትን አልፈልግም ብሎ አሽቀንጥሮ መጣል የያንዳንዳችን የግል ምርጫ ነው። እዚህ ላይ አሽንቀንጥሮ የሚጣለው ኢትዮጵያዊነት፤ አያትንና ቅድመ አያትን፣ ታሪክንና ቅርስን፣ እና ምንነትንና ማንነትን መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

ኢትዮጵያዊ ሆነን የአንድ ሃይማኖት ወይንም የሌላ ሃይማኖት ተከታይ አለዚያም ሃይማኖት አልባ መሆን ችለናል። ኢትዮጵያዊ ሆነን በሀገሪቱ ካሉት ቋንቋዎች የአንዱ ወይንም የሌላው ተናጋሪ መሆን ችለናል። አልፎ ተርፎም አንዳንዶቻችን ከአንድ በላይ ቋንቋ ተናጋሪ መሆን ችለናል። ብዙ ቋንቋዎች መናገር መቻል ይጠቅማል፤ ያኮራል፤ ያስከብራልም። ከሀገር ውጭ የሚነገሩ ቋንቋዎችን ማጥናትና መጠቀም በዓለም ዙርያ ለተበተንነው ኢትዮጵያዊ ስደተኞች ምን ያህል እንደጠቀመን ኑሯችን ይመስክር። "ዕውቀት ባለቤቱን የትም ቦታ የሚከተል ሀብት ነው፤" ይላል የቻይናውያን ጥቅስ። የኢትዮጵያዊነታችን አስተሣሣሪ ክሩ፤ ከኢትዮጵያ ሆነን፤ ለሀገራችን ያለን ፍቅርና ለመላ ኢትዮጵያዊያን ያለን አክብሮት ነው። ለትናንቶቹም፣ ለዛሬዎችም፣ ለነገዎችም። ለታሪኩም፤ ለቅርሱም፤ ለባህሉም።

ከአለፈው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ፤ በሀገራችን በኢትዮጵያ፤ ገዢዎች ቢቀያየሩም፤ እኒህ ገዢዎች የሚከሰትባቸው ችግርና የሚያቀርቡት መፍትሄ አልተለወጠም። ችግሩ አንድ ነውና። እነሱ ራሳቸው። ወታደሮቹ፣ ፖሊሶቹ፣ ዳኞቹ፣ አስተዳዳሪዎቹ በሙሉ መሪዎቻቸውን በማመንና በመከተል፤ ሀገራቸውን ያገለገሉ መስሏቸው፤ ለመሪዎቻቸው መጠቀሚያ ሆነዋል። አሁንም ያው እየተደገመ ነው። እንደዕውነቱ ከሆነ፤ አሁን፤ "ያሁኑ ይባስ" የሚያስብል አዘቅት ውስጥ ነው ያለነው። ያሁኑ የከፋ ነውና።

በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን የትግራይ ሕዝባዊ ነፃ አውጪ ግንባር/ህዝባዊ ወያነ ሀርነት ትግራይ ( ህወሀት ) ወይንም ራሳቸውን በተለምዶ እንደሚጠሩት - ወያኔ - ነው። በመሠረቱ ይህ ድርጅት የትግራይን ወገናችንን ከኢትዮጵያ ገንጥዬ ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተነሣ ድርጅት ነው። የትግራይ ወገናችን ይኼንን እኩይ ዓላማውን ስለአልተቀበለውና አትወክለኝም ስላለው እንቅፋት ሆነበት እንጂ! ***"በትግራይ ክልል ችግር የለም። ችግሩ ሌሎች ስለሆኑ፤ ሌሎችን ከትግራይ አባርሬ፣ እኔ ከላይ ሆኜ የጠቅላላውን የትግራይ ነዋሪ ጥቅም አስጠብቃለሁ ነው"*** የሚለው። ከተፈጠረ ጀምሮ ያለው የፖለቲካ መርሃ ግብሩ የሚያተተው ይኼንኑ ነው። በህወሀት ዕምነት ትግራይና ሌሎች እንጂ ኢትዮጵያዊያን የሚባሉ ግለሰቦች አልነበሩም፤ የሉም፤ አይኖሩምም። በነዚህ ያልተካተተ ደግሞ ወደደም ጠላ ወይ ካባቱ አለያም ከናቱ ዘመዶች መቧደን አለበት። ኢትዮጵያዊነትም ሆነ ኢትዮጵያ፤ በመልክዓ ምድሩም፤ በዘር ክፍፍሉም መዝገብ የለም። ***ኢትዮጵያዊ ነን ባዮች ከመዝገብ ውጭ ነን።*** አሁንም ቢሆን ለፖለቲካ መስኩ፤ የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር በነፃ አውጪነቱ፤ የኢትዮጵያ ገዢነቱ ተቃርኖ ነው። ለምን ከትግራይ ነፃ አውጪነቱ አልፎ ወደ የኢትዮጵያ ፓርቲነት ተሻግሮ በሀገሪቱ የፖለቲካ ማህደር አንድ ተጫዋች አልሆነም ለሚለው ጥያቄ መልሱ ምንድር ነው? ይህ ለህወሀት የሚቀርብ ትክክለኛ ጥያቄ ነው። የፖለቲካ የዋህነት አጫዋቹ ላልሆነ ግለሰብ፤ የጀኔራሎቹ የወያኔ አባላት ብቻ መሆናቸው ሊያስገርም አይችልም። የዋና ዋና ሚኒስትሩን ቦታ የያዙትም እንዲሁ። ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ዕድል የሚሰጣቸውም ጭምር። ቤተክርስትያናትን በተመለከተም። ሂደቱን ተከታትላችሁታል። በደንቡ መሠረት የወያኔ አባላት ትግራዋይ ናቸው።

ይህ የወያኔ ብቻ በሽታ አይደለም። የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር እና የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር ከዚህ የተለዩ አይደሉም። ይህም ማለት፤ ዛሬ ኦነግ ሥልጣን ላይ ቢወጣ፤ የኦነግ አባላት ናቸው የወያኔ አባላትን አባረው ወንበራቸው ላይ የሚወጡት። እዚህ ላይ ለምንአልባቱ ከመገንጠል ተመልሶ፤ ጉልበቱና በቂ አባላት ኖረውት፤ ሀገሪቱን ቢያስተዳድር ከሚል ቅዠት ተነስቼ ነው። በደንቡ መሠረት የኦነግ አባላት ኦሮሞዎች ናቸው። የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር ሥልጣኑን ቢጨብጥም እንዲሁ። በደንቡ መሠረት የኦብነግ አባላት ኦጋዴኖች ናቸው። ይህ በነዚህ ድርጅቶች ብቻ ሣይከለል፤ የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግሬስ፣ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ዕንቅስቃሴ፣ የጋምቤላ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር፤ የአፋር ነፃ አውጭ ድርጅት፣ የቤንሻንጉል ነፃ አውጭ ድርጅት፣ የሲዳማ ነፃ አውጭ ድርጅት፣ የአረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉዓላዊነት፣ የሶማሊያ ዲሞክራሲያዊ ትብብር ኃይሎች በሙሉ የዚህ ዕንስስ ቀመሞች ናቸው። የሕልውናቸው መሠረት "***እኛ ልዩ ነን፤ እነሱ ከኛ ውጪ ናቸው፤ እናም የራሳችን የተለዩ መፍትሄ አለን።***" ስለሆነ ሁሉም አንድ ናቸው።

ወደ ኋላ መለስ ልበልና ታሪካዊ ሂደቱን ላገናዝብ። በአፄው ዘመን የአፄው ቤተሰብ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚኖረውን ወገናችንን መሬት በመንጠቅ ለአባሎቹና ለአቂላቢዎቹ በመሥጠት ነዋሪውን ጢሰኛ አድርጎት ነበር። በአሁኑ ሰዓት ህወሀት እንደሚከተለው ፖሊሲ። በዕርግጥ አሁን መሬት በሙሉ በህወሀት ሥር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረትም በአዜብ በሚመራ የትግራይ መቋቋሚያ ድርጅት ሥር ነው። ለዘመናት

የተጠራቀመ ብሶትና ምሬት በዬቦታው ነበር። የጎጃም ነዋሪ መሬቴን አላስለካም በማለት በበላይ ዘለቀ፣ በደጃች አበረ፣ በሌሎቹ የያዘውን ቁርሾ አዛምዶ፤ ተነስቶ ነበር። በባሌ ዋቆ ተነሥተው ነበር። ታከለ ወልደ ኃዋርያትም ተነሥው ነበር። ይህንን የጠቀስኩት ነጥቡን ለማሥመር ብቻ ስለሆነ የተደረጉትን ሕዝባዊ መነሳሳቶች በሙሉ ለመዘርዘር አልከጅልም። ከወታደሩ በኩል የ፲፱፶፫ቱ መፈንቅለ ሙከራ ተጠቃሽ ሲሆን፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ምን ጊዜም የማያባራው የተማሪው እንቅስቃሴ የራሱ ሥፍራ አለው።

እንግዲህ በዚህ አገሮት በአንድ በኩል በሥልጣን ላይ ያለ ቡድን፤ ለገዢነቱ ሕጋዊነት ለመሥጠት የሀገሪቱን አንድ ክፍል ወካይ ( አፄው አማራውን፤ ህወሀት ትግራዩን )፤ ወይንም ሀገር አቀፍ ወካይ ( ደርግ )፤ መስለው ይቀርባሉ። በሁለቱም ወገኖች ያሉት ገዢዎች ራሳቸውን ከመወከልና በስልጣን ራሳቸውን ለማቆየት የሚችሉትን ከማድረግ አልፈው፤ ሕጋዊነትም ሆነ ሕዝባዊ መሠረት የላቸውም። በአንፃሩም፤ በዚህ ወቅት የዴሞክራሲ ጠብታ እንኳን በሀገሪቱ አለመኖር ለ"ብሔር ነፃ አውጪዎች ግንባሮች" መፈልፈል ፍጉ ነበር። እናም ፈሉ። ይኼንን የሀገር አቀፍ በደል የግል የአካባቢያቸው በደል አድርገው በመነሣት፤ አካባቢያቸውን ነፃ ለማውጣት የነፃ አውጪ ግንባሮች በየቦታው ተፈጠሩ። ባንዳንድ አካባቢዎች ከአንድ በላይ ነፃ አውጪ ግንባሮች አንዱን ክፍል እወክላለሁ በማለት ተፈጥረው ነበር። ቀጥለውም ጠመንጃ አንስተው፤ የአካባቢውን ነዋሪ ማፈንና ማስጨነቅ፤ ወታደራዊ ሥርዓት ማስፈን ግድ አለ። የዚህ ዓይነት ድርጅት፤ በተፈጥሮ ባህርዩ "እኔ ብቻ ነኝ ወካይ" ባይ ነውና፤ አንዱ ሌላውን ማጥፋቱ፤ ሣይታለም የተፈታ ነው። በዚህም ህወሀት ትግራይ ነፃ አውጪ ግንባርን ( ጠርናፊትን )፤ ሸዓቢያ ጀብሃን ማጥፋታቸው ይጠቀሳል።

በዚህ ወቅት የዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሽኩቻ በአሜሪካና በሶቪየት ኅብረት መካከል የተከታዮቻቸውን ጎራ ለማድለብ ሩጫ ነበር። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጠላቴ ነው ያለ ሁሉ፤ በሶቪየት ኅብረት ጎራ በመካተት፤ ከአሜሪካ ጎራ ካለ ሀገር መገንጠልና ነፃ መውጣት፤ መብቱ ነበር። ይህ የሚሰራው በአሜሪካ ጎራ ካሉት እንጅ በሶቪየት ጎራ ያለ ይኼንን ካነሣ አይቀጡ ቅጣት ይቀበላል - ከራሱ ከሶቪየት ጀምሮ፣ በዩጎዝላቪያ፣ በቻይና፣ በቼኮዝላቪያ፣ . . . ወዘተ ሂደቱን አንባቢ ይረዱታል። በዚህ ወቅት ነበር የነፃ አውጪ ግንባሮች በሀገራችን የተቋቋሙት። ከዚህ በመነሣት፤ የራሳቸውን መንግሥት ለመመሥረት፤ የራስ አካባቢ መለየት፣ የራስ ታሪክ መመሥረትና፣ የራስ የባህልና የምጣኔ ሀብት መፍጠር፤ ተከትሎ የሚመጣ ሂደት ነበር። ( ለዚህ አራጋቢ የሆኑት በነዚህ ክልል አቀፍ ድርጅቶች በአመራር የተቀመጡት ሲሆኑ፤ ከአመራር ቢባረሩም፤ የእዕምነታቸው መሠረት ነውና፤ ይዘውት ይጓዛሉ። በዚህ ረገድ ለማስተርስና ለዶክትሬት ቴሲሱ ይኼንኑ የፃፈውን ሁላችን እናውቀዋለን። ) ልዩነትን አጉልቶ፤ የመለያያ ነጥብ አድርጎ ማቅረብ፤ በአብሮነትና በዴሞክራሲ ላይ ጠርነት ማወጅ ነው። ልዩነቶች በመካከላችን ያለውን ቀለም ያበዛዋል። መቻቻልን ያጎለብታል። በአንድ ገፅታ ሊታዩ የማይችሉት አሳዳጊና አልሚ ሃሣቦች ወደ መድረክ እንዲቀርቡ ያደርጋል። እናም በኅብረት ጥንካሬንና ዕድገትን ያስከትላል። ክፍፍል - ኃፍረትን እና የበለጠ ክፍፍልን ያመርታል። ትብብር-ኅብረትንና ተስፋን ይሰጣል። ያሳድጋል። ያበረታታል።

በልዩነት ግን መሠረታዊ የሆነው የግለሰብ መብት ወደኋላ ይገፈተራል። ግለሰቡ ወደደም ጠላ፤ በርዕዩቱና በማህበረሰቡ የኑሮ አደረጃጀት ላይ የተመሠረተ አመለካከት ሣይሆን፤ በሚናገረው ቋንቋና በተወለደበት አካባቢ ላይ የተመረኮዘ የፖለቲካ አስተሳሰብና፤ ***"እኛ ከዚህ፤ ሌሎቹ ከዚያ፤"*** የሚል ዜማ እንዲቃኝ ይገደዳል። ይህ በመሠረቱ፤ ግለሰቦችን በፍላጎትና በዕምነታቸው ሣይሆን፤ በተፈጥሮ አካባቢያቸውና ቋንቋቸው የሚከፍል ዘይቤ ነው። ይህ ደግሞ ከክልል ክልል መለያየትንና በጠላትነት መመልከትን ያስከትላል። በአሁኑ ሰዓት፤ በየአካባቢው ጎሳን ታከ፤ ምጣኔ ሀብትን

ተንተርሶ፤ በገዢው የአመራር ዘይቤ ተደግፎ ግጭቶች መፋፋማቸው የዚሁ መመሪያ ውጤቶች ናቸው። የገዢው ቡድን የራሱን አካባቢ ከሌሎች ማስበለጡ በግንዛቤ ሂደት የሚያስገርም አይሆንም። የሚያስገርመው፤ ሌሎች ይኼ ገዢ ቡድን በተዓምር፤ ሁሉንም የሀገሪቱ ክፍሎች በዕኩልነት እንዲያስተዳድር መጠበቃቸው ነው።

እንግዲህ ከላይ የተዘረዘረውን በልባችን ይዘን፤ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምኅዳር እንቃኝ። ህወሀትና በኢህአዴግ ዙርያ ያሰባሰባቸው የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ የሀገሪቱን አንድ ክፍል ብቻ እያንዳንዳቸው እንወክላለን ባዮች ናቸው። እውነት ይወክላሉን? የሚለውን ለሌላ ጊዜ እንተወውና፤ እንኝህ ድርጅቶች፤ እንወክለዋለን በሚሉት አካባቢ፤ ሕዝቡን በማፈንና በማሰቃየት ላይ መሆናቸውን ጠቅሸ ማለፍ እወዳለሁ። በተለይ ሌላ ድርጅት ባካባቢው እንዳይንቀሳቀስ የማይሸርቡት ተንኮል፤ የማይጠመጥሙት ሸር የለም። የተፈጥሮ ባህሪያቸው ነውና። ሕጋዊነትን አግኝተው፣ ደንቡንና ሥነሥርዓቱን ተከትለው፣ እና የተደነገገላቸውን መብት ተቀብለው የሚንቀሳቀሱት ሕጋዊ ተቃዋሚ አካባቢ ተኮር የፖለቲካ ድርጅቶች፤ በአጀንዳ ከተለጣፊዎቹ ጋር አንድ ቢሆኑም፤ የህወሀት ቡችሎች ባለመሆናቸው፤ ሊያድጉም ሆነ ከሌሎች ጋር ሊተባበሩ አይችሉም። አንድም የተፈጥሮ ባሕሪያቸው፤ ሌላም የህወሀት ተቃርኗቸው ያግዳቸዋልና።

አንድ ነገር ግልፅ መሆን አለበት። እያዳንዱ ኢትዮጵያዊ እየደረሰበት ያለው በደል አንድ አይነት ነው። ኦሮሞው፣ አማራው፣ ሲዳማው፣ ሱማሌው፣ . . . ወዘተ ሁሉም። አሁን በኢትዮጵያ ያለው የኢትዮጵያ መንግሥት አይደለም። እናም ያለው ትግል ለዴሞክራሲ መብት የሚደረግ ትግል አይደለም። አሁን የሚደረገው ትግል በሀገሪቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ለመመሥረት የሚደረግ ትግል ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ከተመሠተ በኋላ ለዴሞክራሲያዊ መብት የሚደረገው እንቅስቃሴ ትርጉም ይኖረዋል። በዕርግጥ ከሥር መሠረቱ ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ የመንግሥት ምሥረታ ትግል፤ ለዴሞክራሲ መብት መንገድ ይሰጣል ብሎ ማመን ከእባብ ዕንቁላል እርግብን መጠበቅ ይሆናል። እንዲህ ያለ መንግሥት ለመመሥረት ግብረገቡም ሆነ ታሪካዊ ግዴታ ያለባቸው፤ ከተቃዊሚው ክፍል የአንድነት ኃይሎች ናቸው። ባሁኑ ሰዓት፤ ሁለቱ የቅንጅት ክፍሎች፤ ማለትም የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትና አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ከየኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ ጋር በመሆን አንድ የፖለቲካ ስብስብ ሲመሠርቱ ነው። እዚህ ላይ ሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ከክልል ትኩረታቸው ወጥተው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ በግለሰብ የፖለቲካ አመለካከት የተመረኮዘ አወቃቀር ይዘው እንዲሰለፉ፤ ማበረታታትና መደገፍ የአንድነት ኃይሎቹ ሊዘነጉት የማይገባ ኃላፊነታቸው ነው።

ይህን ክፍል አንድ በዚህ በተቃዋሚው ወገን ባሉት ያንድነት ኃይሎች መሠባሰብ ግዴታ አስፈላጊነት አስርና፤ በክፍል ሁለት፤ “ትጥቅ ትግልና ለውጥ በአሁኗ ኢትዮጵያ፤” በሚል ርዕስ፤ የትግል ሥምሪቱን እቃኘዋለሁ።